# እጆጆችን የእርሱ ናቸው

ፕሬዘደንት ዲየተር ኤፍ ኡክዶርፍ
የቀዳሚ አመራር ሁለተኛ አማካሪ

በሁለተና የአለም ጦርነት ውጊያ ትልቁ የኢየሱስ ሐውልት እንደተበላሸ ታሪክ ይናገራል። የከተማው ሰዎች ሀውልቱ መበላሸቱን ካወቁ በኋላ አዘኑ ምክንያቱም የምነታቸው ምልክት እና እግዚአብሄር ከነሱ ጋር እንደሂነ የሚያሳይ ስለነበረ ነው።

ባለሙያዎች ሀውልቱን ጥግኖት ነበር ግን እጁ በጣም ስለተበላሸ ልተገን አልቻለም። አድስ እጅ እንድሰራም ሙያተኛ እንድቀጠር አንዳንዶቹ አስተያየት አደረጉ። ሌሎች እንዳለ እንድሆን ፈለጉ። እናም ሀውልቱ የለ እጅ ቀረ። የከተማው ሰዎች የኢየሱስ ክርስቶስ ሀውልትት አንቴ እጄ ነህ በሚለው ቃል ጨመሩበት።

ይህ ጥልቅ ያለው የታሪክ ትምህርት ነው። ስለክርስቶስ ሳስብ እጁን በመዘርጋት ማፅናናት፤ ማዳን እና የሚፈቅር እንደሆነ አስባለሁ። የተቸገሩትን በመውደድ በመሀከላቸው ሄደው ሞኞትን እና ደንነትን አስተምረዋል።

በሥጋው ህይወቱ ይህን ነው ያደረገው፤ ዛሬም በኛ መሀከል ቢሆን ይህን ያደርጋል። እኛም እንደ ተከታዩነታችን እና የኋላኛው ቀን ቅዱሳን የኢየሱስ ከርስቶስ ቤተክርስትያን አባልነታችን እህን ማድረግ እንዳለብን ነው።

በዚህ ቆንጆ ፋስካ ጠዋት ልባችን እና ሀሳባችን ወደ ኢስራኤል ተስፋ እና የአለም ብርሀን መሳብ አለበት።

እሱ የኛ ፍፁም ምሳሌ መሆኑን ስናሰላስል እጃችን እና አይናችን የእሱ እናደሆነ ማሰብ አለብን።

የቤተክርስትያን አባላችን ሌለሎች በሚሰጡት አገልግሎት በጥልቅ ተገረምኩኝ። ያለራስ ወዳድነት ሌለሎች የሚታደርጉትን አስተዋፅኦ ስንሰማ ልባችን በምስጋና ያበጠ ይሆናል። ለአለማት የሚታንፀባርቁ ብርሀን ናችሁ። ለደግ ሥራና ርህራሄ ታውቃችዋል።

ከጊዜ ወደ ጊዜም የቤተክርስትያን አባሎች ተስፋ በመቁረጥ ወደ ቤተክርስትያን ባለመምጣት ተካፋይ አለመሆናቸውን እንሰማለን።

በሁለተኛው የአለም ጦርነት ልጅ በነበርኩ ጀርመን ለሁለት ተካፍላ ነበር። ብዙ ሰዎች በረሀብ እና በሽታ እየሞቱ ነበር። ከሶልት ሌክ ከተማ ቤተክርስትያን እርዳታ መምጣቱን በደንብ አስታውሳለሁ። እስካሁንም የልብስ ሽታ እና በጣሳ ኮክ ጣፋጭነትን አስታውሳለሁ።

አንዳንዶቹ በተቀበሉት ምግብ ምክንያት የቤተክርስትያን አባል የሆኑ ነበሩ። አንዳንድ የቤተክርስትያን አባሎች አድስ አባሎችን በዝቅተኛነት ተመልክተው ነበር። የታሸገ ምግብ ሞርሞን በማለት አስቀያሚ ስምም ሰጥቶአቸው ነበር። እነኝህ አድስ አባሎች ግዜያዊ ችግራቸው ከተሟላ በኋላ ቤተክርትያን እንደሚለቁ ብለው ያምኑ ነበር።

ጥቅቶቹ ብሄዱም ብዙዎቹ ወደ ቤተክርትያን በመምጣት የወንጌልን ጣፋጭነት ቀመሰዋል። የእግዚአብሄር መንግስት ቤታቸው እነደሆነ ተገነዘቡ። ከሶስትና አራት ትውልድ በኋላ ብዙ ቤተሰቦች አባልነታቸውን ወደዝሁ ይመለከታሉ።

በአለባበስ፤ በንግግር እና ነገሮች በልዩነት የሚያደርጉትን የግዚአብሄር ልጆች እንኳን ደህና መጣችሁ እንደምንል ምኞተ ነው። ሌሎችን እንደተጎደሉ መመልከት ጥሩ አይደለም።

ዳኝነት ለመስጠት ስንሳሳት አዳኝን እናስታውስ፤ ምክንያቱም ዓለምን ወደዋል፣ ሰዎችን ሁሉ ወደ እርሱ ይስብ ዘንድም ሕይወቱን አሳልፎ ሰጠ። እርሱ እንዲህ ይላል፡- ከምድር ዳርቻ ሁሉ ወደ እኔ ኑ፣ ያለገንዘብም ያለዋጋም ወተትና ማር ግዙ። እሱም አለ በምድር ዳርቻ ያላችሁ ሁሉ ወደ እኔ ኑ፤ ግን ሁሉም ሰው እንደሌላው ታድሏል፤ እናም ማንም አልተከለከለም።

መፅሀፍ ቅዱስ ሳነብ በሀብትና በቅዱስ ተሰሚነት እራሳቸውን ከፍ በማድረግ ጌታን የሚቀርቡ እንዳሉ ይታያል።

በአንድ ወቅት አዳኝ ወደ ቤተመቅደስ ለመፀለይ የመጡትን ሁለት ወንዶች ይህን ምሳሌ እንዲህ ስል ነገራቸው።

ሁለት ሰዎች ሊጸልዩ ወደ መቅደስ ወጡ፥ አንዱ ፈሪሳዊ ሁለተኛውም ቀራጭ። ፈሪሳዊም ቆሞ በልቡ ይህን ሲጸልይ። እግዚአብሔር ሆይ፥ እንደ ሌላ ሰው ሁሉ፥

ቀማኞችና ዓመፀኞች አመንዝሮችም፥ ወይም እንደዚህ ቀራጭ ስላልሆንሁ አመሰግንሃለሁ፤ በየሳምንቱ ሁለት ጊዜ እጦማለሁ፥ ከማገኘውም ሁሉ አሥራት አወጣለሁ አለ።

ቀራጩ ግን በሩቅ ቆሞ ዓይኖቹን ወደ ሰማይ ሊያነሣ እንኳ አልወደደም፥ ነገር ግን። አምላክ ሆይ፥ እኔን ኃጢአተኛውን ማረኝ እያለ ደረቱን ይደቃ ነበር። እላችኋለሁ፥ ከዚያ ይልቅ ይህ ጻድቅ ሆኖ ወደ ቤቱ ተመለሰ፤ ራሱን ከፍ የሚያደርግ ሁሉ ይዋረዳልና፥ ራሱን ግን የሚያዋርድ ከፍ ይላል።

ሁሉ ኃጢአትን ሠርተዋልና የእግዚአብሔርም ክብር ጎድሎአቸዋል፤ ሁላችንም ምህረት ያስፈልገናል። በመጨረሻው ቀን በእግዚአብሄር ዳኝነት ስንቀርብ ስህተታችን እንድስረፅልን አንፈልግም? ጌታን ለማቀፍ አንፈልግም?

ለራሳችን የሚንፈልገውን ሌለሎችም ማድረግ አግባብና ትክክል ነው።

ሀጢአትን መቀበል ወይም እርኩስን መመልከት አለብን ማለቱ አይደለም።አንዳንዴ በፋልጎታችን ሀጢአተኞችን ያለርህራሄ በፍጥነት እናወግዛለን። ከዘመኑ ራዕይ እንደምንረዳው  የነፍስ ዋጋ በግዛብሄር ፍት ታላቅ እንደሆነ እናውቃለን። ከሁለንተና የበለጠ የሌሎችን ነፍስ መለካት  አንችልም። የሚንገናኛቸው ሰዎች ሁሉ ለሰማይ አባት በጣም ጠቃም ናቸው። ይህን ከተረዳን ሌሎችን ማስተናገድ መረዳትን  እንጀምራለን።

**ለአመታት ችግርና ሀዘን የደረሰባት ሴት በንባዋ እንድህ አለች፤ እንዴ አሮጌው ሀያ ዶላር የተጨማደድኩ ብሆንም ሀያ ዶላር ነኝ ። ዋጋ አለኝ። ብዙ ባልመስልም እና በመጨማደድ ብጠቀምም ሀያ ዶላር ሙሉ ነኝ።**

ይህን በማስታወስ ማናቸውም በችግር መንገድ የሚጓዙ ስለሆነ በርህራሄ ልባችንና እጃችን እንዘርጋ። እንደ ክርስቶስ ተከታይነታችን ከማስወገዝ እርዳታ እናድርግ።  ከሚያዝኑኑት ጋር ማዘን እና ፅናት የሚያስፈልጋቸውን ማፅናናት እንዳለብን ታዘናል።

እንደ  ክርስትያን የሚሰቃዩት መሰቃየት ይገባቸዋል ማለት ብቁነት አይደለም። በጌና ሰንበት ማስታወስ ጥሩ ነው። አዳኛችን በፈቃዱ የሁሉን ሰዎች ህመምና ስቃይ በራሱ ላይ ወስደዋል፡

በመፅሀፈ ምሳሌ- ወዳጅ በዘመኑ ሁሉ ይወድዳል፤ ወንድምም ለመከራ ይወለዳል። ሁል ጊዜ ወዳጅ እንሁን። በመከራ ጊዜም ለወንድም እና እህቶች ደራሽ እንሁን።
አንድ የይሁዳ ሽማግሌ በማሳ ውስጥ አንድ ላይ የሰሩትን ወንድሞች እንድሁ አልቸው፡- ምርቱን በእኩል እንድካፈሉ ተስማሙ። አንድ ሌሊት መከር እየተቃረበ ስመጣ ዙሚር መተኛት አልቻለም፤ ምክንያቱም አብራም ባለቤትና ሰባት ወንድ ልጆች የነበረው ግማሹን መቀበል እና እሱ ብቻውን ብዙ ስላለው መተኛት አልቻለም።

እና ዙሚር በመልበስ ወደ ማሳ በመሄድ ሶስት እጅ በውንድሙ ክምር ላይ ካስቀመጠ በኋላ በእርካታ ወደ መኝታው ተመለሰ።

አብራምም እንደዝሁ ደሀው ወንድሙ የሚረዱት ልጆች ብሎ በማሰብ መተኛት አልቻለም። ዙሚር እንደዚህ በድካም የሰራ ግማሽ ማግኘት ትክክል አይደለም። በውነትም ይህ እግዚአብሄርን አያስደስትም። እና አብራም በቀስታ ወደ ማሳ በመሄድ ሶስት እጁን ለምወደው መንድሙ ክምር ላይ አደረገ።

በሚቀጥለው ጠዋት ሁለቱም ወንድሞች ወደ ማሳው ሄደው ባዩት ክምር መጠን ተገረሙ። ያን ሌሊት ሁለቱም ወንድሞች የበፍቱን ሁነታ እንደዚሁ ደገሙ። ይህን ጊዜ ስላወቁ በለቅሶ ተቃቀፉ። ሁለቱምልባቸው በፍቅርና ምስጋና ስለተሞላ መናገር አልቻሉም።

**ይህ የመንፈስ ርህራሄ ስለሆነ ሌሎችን እንደራሳችን መውደድ አለብን። ደስታቸውን እንደ እራሳችን መፈለግ አለብን።**

እውነተኛ ፍቅር ድርጊትን ይጠይቃል። ስለ ፍቅር ቀኑን ሙሉ ማውራት ፤ መስታወሻ ወይምግጥም መፃፍ፤ መዘመር ወይም መስበክ ብንችልም ከፍቅር ድርጊት ውጭ ልሆን አይችልም።

ክርስቶስ ስለ ፍቅር መናገር ብቻ ሳይሆን ዕድሜውን ሙሉ አሳይተዋል። እራሱን ከህዝቦች አልገነጠለም። በመሀከላቸው በመሆን ደረሰላቸው። የጠፉትን አዳነ። ሌሎችን መርዳት ማስተማር ሳይሆን ስለ ሥራው ሌሎችን ወኪል ሰጠ። እንዴት ማድረግ እንዳለብን ማስተማር ብቻሳይሆን አሳየን።የሚንጠለጠለው እጅ በማንሳት ለሽባውን እግር ብርታት ስጡ።

ክርስቶስ ሌሎችን እንደት ማስተማር እንዳለብን ያውቃል። ክርስቶስ እጁን በመዘርጋት የነካቸው ብርታት በማግኘት የተሻሉ ሰዎች ሆኑ።

የእሱ እጅ ከሆን እንደዚሁ መስራት የለብንም?

አዳኝ ስለቤተሰባችን፤ ዎርዳችን እና ህዝባችን ፍፁም ልዩ የሆነን ገልፀዋል። ፍቅር ታላቅ ትዛዛት እና የነቢያት ቃሎች የሚንጠላጠሉበት ነው። ስለ ህይወት ሁነታዎችን በጥልቀት በማሰብ ጊዜያችን ማሳለፍ እንችል ልሆን ይችላል። ግን ታላቅ ትዛዝን ችላ አድርገናል፤ ፍሬ ነገሩን አጥነናል፤ ዳመና ካለውሀ እንደሚንጠባጠብ እና ዛፍ ከለ ፍሬ እንደሆነ ነው።

አዳኝ ስለ ታላቁ ትዕዛዝ በተናገረ ወቅት ስለኑሮአችን እና በታችን አስፈላጊነት ገልፀዋል። ኢየሱስም እንዲህ አለው። ጌታ አምላክህን በፍጹም ልብህ በፍጹም ነፍስህም በፍጹም አሳብህም ውደድ።
 ታላቂቱና ፊተኛይቱ ትእዛዝ ይህች ናት። ሁለተኛይቱም ይህችን ትመስላለች፥ እርስዋም። ባልንጀራህን እንደ ነፍስህ ውደድ የምትለው ናት። በእነዚህ በሁለቱ ትእዛዛት ሕጉም ሁሉ ነቢያትም ተሰቅለዋል።

ከእግዚአብሄር ፍቅር እና ጓደኞቻችን ውጭ እኛ ቤተክርስትያን እንጂ አላማ የሌሌን ሰዎች ነን።

 ፍቅር ነው የሰማይ አባት መንፈሳችን እንድፈጥር ያደረገው፤ ፍቅርም ነው አዳኛችን ለኛ ሀጢአት ወደ ገትሰመን ጓሮ የመራው። ፍቅር የደህንነት ዕቅድ መሰረታዊ አነሳሽ ነው። የደስታም ምንጭ፤ የፀደይ ማዳኛ እና የተሰፋ ዕንቁ ምንጭ ነው።

በክርስቶስ ፍቅር እጃችን እና ልባችን ሌለሎች ስንዘረጋ ቆንጆ ሁነታ ይሆንልናል። መንፈሳችን በመዳን ብርታት እናገኛለን። የበለጠ ደስተኞች እና ሰላም ይኖረናል፤ እናም መንፈስ ቅዱስ ተቀባይም እንሆናለን።

የሰማይ አባት ለኛ ለሰጠው ፍቅር እና ልጁ ኢየሱስ ክርስቶስ ምሳሌና ያለሀጢአት አስተተዋፅኦ ማድረግ በሙሉ ልቤና ነፍሴ ምስጋና እሰጣለሁ። ኢይሱስ ያልሞቴ ሳይሆን ግን ከመቃብር በመነሳቱ እደሰታለሁ። ኗሪ በመሆኑ ወደ ምድር በመመለስ ወጌሉን እና ሥልጣኑን እንድገና ለሰዎች መልሰዋል። ምን መሆን እንዳለብ ፍፁም የሆነ ምሳሌ ሰትቶናል።

**በዚህ ፍስካ እለት እና ሁል ጊዜ አዳናችን እንደት እንድያዘን በፀጥታ ማስላሰል …እጁ ለመሆን እንወስን። ለሎችም ይህን በማየት ፍቅሩን እንድሰማቸው ይሁን። በኢየሱስ ክርስቶስ ስም አሜን።**